# <u>የግንቦት 20 በአል በቤይጂንግ የኢትዬጵያ ኤምባሲ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ</u>

ኢትዬጵያ ኤምባሲ፣ቤይጂንግ ግንቦት 20 ቀን 2006 ዓ.ም. - በሀገራችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ የተጀመረበት 23ኛው የግንቦት 20 በአል የኢትዬጵያ ኮሚዩኒቲ አባላትና በቤይጂንግ የኢትዬጵያ ኤምባሲ ባልደረቦች በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

በበአሉ ላይ የኤምባሲው ምክትል ሀላፊ የሆኑት ክቡር አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ ባደረጉት ንግግር፤ "ሀገራችን የተያያዘችውን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ ፅኑ መሠረት ያለው ለማድረግ እየተካሄደ ያለው የፈጣን ልማትና የተቋም ግንባታ ሂደት ዛሬ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ መድረሱን በዓሉን ስናከብር ልናሰምርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ባለፉት 23 ዓመታት የተጓዝነውን ርቀትና ያገኘነውን ልምድ በመቀመር በቀጣይ ጉዟችን ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንደምናሰልፍ ያለጥርጥር መናገር ይቻላል" ብለዋል፡፡

አክለውም የአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በመልካም ሁኔታ እየተከናወነ እንደሚገኝ አውስተዋል፡፡ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ስራ 33% መጠናቀቁን አስታውሰው በቀጣይም ይህ በሀገር ሀብትና ብሄራዊ መግባባት እየተከናወነ ያለ ስራ ፍፃሜ ላይ እንዲደርስ በቻይና የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድጋፋቸውን አጠናክረው ለመቀጠል ቃላቸውን የሚያድሱበት አጋጣሚ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡ (የንግግሩን ሙሉ ቃል ይመልከቱ)





በበአሉ ላይ የታላቁን የህዳሴ ግድብ ቦንድ በመግዛት አስተዋፅኦ ላበረከቱ የኢትዬጵያ ኮሚዩኒቲ አባላትና የኤምባሲው ባልደረቦች በኤምባሲው የተዘጋጀ የምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

በቤይጂንግና በአካባቢው የሚገኙ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባላት ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ቢሆንም በድምሩ 164,550 የአሜሪካ ዶላር በቦንድ ግዥና በስጦታ ያበረከቱ መሆኑ ተገልፆል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቻይና በትምህርት ላይ የሚገኙ የመከላከያ ሚኒስቴር ባልደረቦች ከተማሪ አበላቸው ላይ በመቀነስ 3,400 የአሜሪካ ዶላር ለማዋጣት ቃል ገብተዋል፡፡

በበአሉ ላይ በኤምባሲው የተዘጋጀው የእራት ግብዣ ከተፈፀመ በኋላ የበአሉ ታዳሚዎች በተለያዩ የኢትዬጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሙዚቃዎች በመታጀብ በአሉን በልዩ ድምቀት አክብረዋል፡፡